# አቡነ ሰላማ




የተስፋ ልጆች

BROTHERS OF SAINT JOHN
ADDIS ABEBA

**Already edited collections of "Children of Hope"**

- እራሴን ለእግዚአብሔር አምልኮ አዘጋጃለሁ (ቀይ)
- ፈጣሪና አባት የሆነው የእግዚአብሔር መገለጥ(አረንጓዴ)
- ዘወትር ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስ ፍቅር(ቢጫ)
- ለቅዱስ ቁርባን አምልኮ የተዘጋጀ ጸሎት(ብርቱኳን)
- ሥዕላዊ የቅዳሴ መጽሐፍ(ወይንጠጅ፣ ሰማያዊ)
- ኑ እና ከኢየሱስ ጋር ተዋወቁ፤ለቅዱስ ቁርባን አምልኮ የተዘጋጀ ጸሎት(ብርቲኳን)
- እማሆይ ተሬዛ (ጥቁር ሰማያዊ)
- ፍራንቸስኮስ (ሼዥ)
- ቅድስት ማርያም
- ባኪታ (ብርቲኳን)
- ወንጌል ከእንስሶች አፍ
- ከኢየሱስ ጓደኞች ጋር እንጸልይ
- እራሴን ለሚስጢረ ንስሐ አዘጋጃለሁ
- የኢየሱስ የህይወት ታሪክ በአጭሩ
- ጸሎት ወደ ማርያም
- የቤተክርስቲያን ጸሎቶች
- አርመናዊቷ አርሴማ
- ወንጌል ለህፃናት





ፍሬሚናጦስ የሮማው ንጉሠ ነገሥት ቆንስጠንጢኖስ ገዢ በሆነበት ወቅት በጢሮስ በ4ኛው ክፍለ ዘመን ተወለደ።


ሞርፊየስ በጢሮስ የሚኖር ክርስቲያን የሆነ ፈላስፋ እና ሀኪም ሲሆን፣ ከፍሬሚናጦስ እና ከወንድሙ ኤዲሲየስ ቤተሰቦች ጋር ቅርበት ያለው ሰው ነበር። ከፍሬሚናጦስ እና ከወንድሙ ኤዲሲየስ ጋር በመሆን ረጅም ጉዞን ወደ ኢትዮጲያ አደረገ። የጉዞው ዓላማ የሀገሪቷን የመሬት አቀማመጥ ለማጥናት እና የሚያገኛቸውንም ሰዎች ስለ ምስራቹ ቃል ለመስበክ ነበር።



ሦስቱ ተጓዦች በመርከብ ተጉዘው የኢትዮጲያ ወደቦች ደረሱ፤ እነርሱም የተፈጥሮአዊ ውበትን በማየት ተመሰጡ፤ አደነቁም፡፡ እነዚህ ሦስት ተጓዦች ተፈጥሮን ሲያደንቁ፣ ሲያሰላስሉ እና ሲያጤኑ ቆዩ፤ ያዩትን እና ያገኙዋቸውን ግኝቶች ሁሉ በጥንቃቄ ከመዘገቡ በኋላ ሞርፌየስ የትውልድ ቦታቸው ወደ ሆነችው ወደ ጢሮስ ለመመለስ ወሰነ፡፡



እነርሱም አንድ ጀልባ ተኮናተሩ እና ቀይ ባህር ላይ ወደ ምትገኘው ወደ ምፅዋ ወደብ መውጣት ጀመሩ፡፡ ነገር ግን እረፍት ለማድረግ በቆሙበት ቦታ ጀልባዋ እና ተጓዦችዋ ላይ ወንበዴዎች ጥቃት አደረሱ፡፡ ሞርፌየስ በሦስት ወንበዴዎች ተገደለ፡፡ ሁለቱን ልጆች ዛፍ መካከል ተደብቀው አገኙዋቸው እና አዳኑዋቸው፤ ነገር ግን እስረኛ አድርገው ወስደው ለአክሱም ንጉሥ አሳልፈው ሰጡዋቸው፡፡








የሁለቱ ወንድማማቾች ጥበብ እና ፀባይ የንጉሡን ልብ አሸነፈ ታልቅ ክብርንም አገኙ፡፡

ኤዴሲዮስ የንጉሡን ፅዋ አሳላፊ እንዲሆን ኃላፊነት ተሰጠው፤ ይህም ማለት ለንጉሡ የሚቀዳለትን ማንኛውንም ዓይነት መጠጥ የሚከታተል ሰው ማለት ነው፡፡

ፍሬሚናጦስን ደግሞ ንጉሡ ጥበበኛነቱን እና የመንፈስ ንቃቱን በማስተዋል፤ ንብረትን ማስተዳደር እና የፅሁፍ ሥራን መከታተልን በኋላፊነት ሰጠው፡፡




ከጥቂት ዓመቶችም በኋላ ንጉሡ ሞተ:: የንጉሡ ልጅም ገና ትንሽ ነበር:: ንግሥቲቱም እጅግ ግራ ስለገባት ፍሬሚናጦስን እና ኤዲሲዮስን “አባካችሁ ተስመኑኝ እና ከእኔ ጋር ኑሩ:: የእናንተ እውቀት ልጄን ለማስተማር እና ግዛቱን ለማስተዳደር ያስፈልገኛል” አለቻቸው:: የእርሷን በእነርሱ ላይ ያሳትን እምነት በማየት ሳያንገራግሩ ጥያቄዋን ተቀበሉዋት::



የንጉሡ ቤተሰብ ፍሬሚናጦስ ላይ ትልቅ እምነት ስለነበራቸው የመንግሥቱ ቁልፍ በእጁ ነበር፡፡ እግዚአብሔርም ፍሬሚናጦስ በታላቅ ጥንቃቄ ከሮም እና ከቤዘንታይን ለንግድ ወደ ኢትዮጺያ ከሚመጡት ነጋዴዎች መሀከል ክርስቲያን የሆኑትን እንዲመርጥ ነገረው፡፡



እርሱም በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት እነዚህን ክርስቲያን የሆኑ ነጋዴዎች ቤተክርስቲያን እንዲሠሩ ጋበዛቸው፤ በተሠራው ቤተክርስትያን ውስጥም አማኞች ተሠብስበው መዝሙረ ዳዊትን ይጸልዩ ነበር፡፡





ፍሬሚናጦስ ጉዞውን ከማጠናቀቁ በፊት በአሌክሳንደሪያ አዲስ ለተሾሙት ጳጳስ አጥናሲዮስ ያጋጠመውን ድንቅ ነገር በምስክርነት አቀረበ፡፡ ጳጳሱ በንቃት እና በመልካም ሰላዳመጡት በመበረታታት “አንድ ብቁ የሆነ እረኛን መርጠው ወደ ኢትዮጲያ ላኩ” ብሉ ሃሳብ አቀረበላቸው፤ ምክንያቱም “በኢትዮጲያ ብዙ ክርስቲያን አማኞች እየመጡ ስለሆነ ይህንን እምነታቸውን እንዲንከባከቡ እና እንዲያሳድጉ በአስቸኳይ ሰው ይላክላቸው እንጂ ችላ ማለት የለብንም” ብሉም ተናገረ፡፡





ጳጳሱ የፍሬሚናጦስ እምነት እና የነገራቸው ነገር ውስጣቸውን ስላሸነፈው “በጌታ ከሚመራው ከፍሬሚናጦስ ውጭ ይህንን ከባድ ኃላፊነት የሚወጣ ሌላ ሰው ከየት እናገኛለን?”ብለው ጠየቁ፡፡

የአሌክሳንደሪያው ጳጳስ ፍሬሚናጦስን ጳጳስ አድርገው ቀቡ፤ ከዚያም ፍሬሚናጦስ ወደ መጣበት ወደ ኢትዮጲያ በእግዚአብሔር ፀጋ ለሰዎች ወንጌልን እንዲሰብክ እና እንዲለውጣቸው ተላከ፡፡



ፍሬሚናጦስ ከታላቅ ደስታ ጋር ወደ ኢትዮጲያ ተመለሰ፤ “አቡነ ሰላማ” እያሉ ይጠሩት ነበር፡፡ ትርጉሙም “የሰላም አባት” ማለት ነው፡፡



እግዚአብሔር ለእርሱ ጥልቅ የሆነ ሰላምን ሰጠው፡፡ብዙ ወንበዴዎችን እና ኢትዮጲያውያንንም ወደ ክርስትና ኃይማኖት አመጣ፤ ብዙ ቤተክርስቲያኖችንም አስገነባ፤ ልክ እንደ ሐዋሪያቶችም ብዙ ተዓምራትን አደረገ፤ ስለ እግዚአብሔርም ታላቅነት በብዙ መሰከረ፤በሚያንፀባርቅ ፍቅር እና በፍፁም ሰላም ይኖር ነበር፡፡





የጢሮሱ ፍሬሚናጦስ ጳጳስ ከሆነበት ጊዜ አንስቶ እንደ ባሪያ ሆኖ ሲያገለግል ቆዩ፤ ብዙ የስብከተ ወንጌል ሥራዎችን በኢትዮጲያ ከሠራ በኋላ በሰላም አረፈ፡፡ እርሱ በቅንዓት እና በቅንነት ያገለገለውን የኢትዮጲያን ህዝብ እና የክርስቶስን መስቀል ትቶ ተሰናበተ፡፡



በደስታ ድምፅ ሰላማ ስላም እልሃለሁ፣

ከፍ አደርግሃለሁ፣ በአንተም እነቃቃለሁ፡፡

ሰላማ የምህረት እና የይቅርታ በር ነህ፣

ደብዛዛ እና ጭለማ ቢሆንብህ፣

በክርስቶስ ብርሃን በኢትዮጲያ ላይ አንፀባረቅህ፡፡



## አጭር የህይወት ታሪክ

ቅዱስ ፍሬሚናጦስ ወይንም በአማርኛ በሚጠሩት አባ ሰላማ፤ በ4ኛው ክፍለ ዘመን የኖሩ የሶሪያ ሀገር ሐዋሪያ ሲሆኑ፤ ለመላው ኢትዮጵያ ክርስትናን ሰብከዋል፡፡ ቅዱስ ፍሬሚናጦስ የመጀመሪያ የአክሱም ጳጳስ ሲሆኑ በኢትዮጲያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ስለ አርዮስ ግንዛቤ እንዲኖር አድርገዋል፡፡

## የእርሳቸው ዓመታዊ ክብረ በዓል

ኦክቶበር 27 በሮማ ቤተክርስቲያን

ኖቬንበር 30 በምስራቃዊያን ቤተክርስቲያን

ዲሴምበር 18 በኮፕት ቤተክርስቲያን ነው፡፡

Acknowledgments
Drawings and text: Abba Athanase csj and Anne-Catherine David
Translation: Abju, Sisay

Printed by:
View Graphics & Printing Plc
011 661 40 07



የተስፋ ልጆች
Children of Hope
ትሬዛ
ቅድስት ማርያም
ባኪታ